መልእክት ሁለት

## ሁለቱ ዛፎች እና ሁለቱ የመኖር መርሆች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 2፡9፤ ዕብ. 4፡12፤ 1 ቆሮ 2፡14-15፤ ሮሜ 8፡4፣ 6፤ ኤፌ. 4፡18-19፤ 2 ቆሮ. 11፡3

**I. በዘፍጥረት 2፡9 ያሉት ሁለት ዛፎች—የሕይወት ዛፍ እና ክፉና መልካምን የሚያስታውቀው የእውቀት ዛፍ—ሁለት የመኖር መርሆችን ይወክላሉ፦**

ሀ. ሁለቱ ዛፎች አንድ ክርስቲያን በሁለት የተለያዩ መርሆች መሠረት ሊኖር እንደሚችል ያሳያሉ—የትክክል እና የስህተት መርህ ወይም የሕይወት መርህ—1 ቆሮ. 8፡1።

ለ. ክርስቲያን መሆን የትክክል እና የስህተት መርህ ጉዳይ፣ የክፉ ወይም የመልካም መርህ ጉዳይ ሳይሆን የሕይወት ጉዳይ ነው—1 ዮሐ. 5፡11-13፣20።

ሐ. ጌታ ኢየሱስን ስንቀበልና አዲስ ሕይወት ስናገኝ፣ ሌላ የመኖር መርህ አገኘን—የሕይወት መርህ፤ ይህን መርህ ካላወቅን፣ የሕይወትን መርህ ወደ ጎን ትተን የትክክል እና የስህተት መርህን እንከተላለን።

መ. ክርስቲያን መሆን አንድ ነገር ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን የመጠየቅ ጉዳይ አይደለም፤ አንድ ነገር በምናደርግበት ጊዜ በውስጣችን ያለውን ሕይወት የመከታተል ጉዳይ ነው—ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ. 4፡18-19።

**II. የክርስትና ሕይወታችን በውስጣዊ ሕይወት የሚመሠረት እንጂ ውጫዊ በሆነ የትክክል እና የስህተት መስፈርት ላይ የሚመሠረት አይደለም፤ የኑሮ መርሆአችን ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ነው፦**

ሀ. በትክክል እና በስህተት መርህ ከኖርን ከዓለማዊ ሰዎች ጋር አንድ አይነት ነን—ቁ. 17።

ለ. ትክክል እና ስህተት የሚወሰኑት በውጫዊ መስፈርት ሳይሆን በውስጣዊው ሕይወት ነው።

ሐ. ክፉ የሆነውን ብቻ ሳይሆን መልካም የሆነውንም ነገር ማስወገድ አለብን፦

1. ክርስቲያኖች ሊያደርጉ የሚችሉት ከሕይወት የሚወጣውን ነገር ብቻ ነው፤ ክፉ ነገሮች፣ መልካም ነገሮች እና የሕይወት ነገሮች አሉ—ዮሐ. 1፡4፤ 10፡10፤ 1 ዮሐ. 2፡25፤ 5፡13።
2. በዘፍጥረት 2፡9 “መልካም እና ክፉ” በአንድ ላይ እንደ አንድ መንገድ ተቀምጠዋል፣ “ሕይወት” ግን ሌላ መንገድ ነው።
3. ከመልካም መስፈርት ከፍ ያለ መስፈርት አለ፤ ይህ መስፈርት ሕይወት ነው—ዮሐ. 11፡25፤ 1 ዮሐ. 5፡11-12።
4. የክርስቲያን ኑሮ መስፈርት ክፉ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን መልካምና ትክክለኛ ነገሮችንም ያስወግዳል።
5. በሰው መስፈርቶች መሠረት ብዙ ነገሮች ትክክል ናቸው፣ መለኮታዊው መስፈርት ግን እነዚህ ትክክል እንዳልሆኑ ይናገራል፣ ምክንያቱም መለኮታዊው ሕይወት የላቸውም።

መ. የክርስቲያን ኑሮ የሚመሠረተው በውስጣዊው ሕይወት ነው—ሮሜ 8፡2፣ 6፣ 10-11፦

1. ማንኛውም ክርስቲያን ከሕይወት ውጭ ነገሮችን መወሰን የለበትም—1 ዮሐ. 5፡13።
2. የውስጡን ሕይወት የሚጨምር ነገር ሁሉ ትክክል ነው፣ የውስጡን ሕይወት የሚቀንስ ነገር ሁሉ ስህተት ነው።
3. መንገዳችን የእግዚአብሔር ሕይወት ነው እንጂ ትክክል እና ስህተት አይደለም፤ በእነዚህ ሁለት መርሆች መካከል ያለው ልዩነት በጣም ሰፊ ነው፣ ንጽጽሩም ታላቅ ነው።
4. ልንጠይቀው የሚገባ ዋናው አንድ ጥያቄ በውስጣችን ያለው መለኮታዊ ሕይወት ከፍ ወይም ዝቅ ማለቱን ነው፤ የምንመርጠውን መንገድ ሊወስን የሚገባው ይህ ነው።
5. እግዚአብሔር መለኮታዊውን ሕይወት እንድናረካ ይጠይቃል፤ እግዚአብሔር የሰጠንን ሕይወት በሚያረካ መንገድ ነገሮችን ልናደርግ ይገባል—ዮሐ. 1፡4፤ 3፡15።
6. እንደ ክርስቲያኖች፣ ለሠራናቸው ኃጢአቶች ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ መግባት የለብንም፤ አብዛኛውን ጊዜ ላደረግናቸው መልካም ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ መግባት ያስፈልገናል።
7. የኑሯችን መርህ ክፉንና መልካምን የሚለየው መርህ አይደለም፤ ከሕይወት የሆነውን እና ከሞት የሆነውን ለማወቅ በእግዚአብሔር ፊት መምጣት አለብን—ሮሜ 8፡6፤ 1 ዮሐ. 3፡14።

**III. በሕይወት መርህ መሠረት መኖር ከፈለግን፣ መንፈስን ከነፍስ መለየት እና መንፈሳችንን ማወቅ አለብን—ዕብ. 4፡12፤ 1 ቆሮ. 2፡14-15፦**

ሀ. መንፈስ የሆነው ጌታ በመንፈሳችን ውስጥ እየኖረ፣ እያደረ፣ እየሠራ፣ እየተንቀሳቀሰ እና እያደረገ ነው፣ እኛም ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ነን—2 ቆሮ. 3፡17፤ ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፦

1. ተግባራዊ በሆነ መንገድ ጌታን ማወቅና በየዕለት ሕይወታችን መለማመድ ከፈለግን መንፈሳችንን መለየት መማር አለብን—2፡14-15።
2. መንፈሳችንን ካላወቅን በውስጣችን የእግዚአብሔርን እንቅስቃሴ መረዳት አንችልም፣ ጌታን መከተልም አንችልም፣ ምክንያቱም ጌታ በመንፈሳችን ውስጥ የሚኖር መንፈስ ነው—1 ዮሐ. 2፡27፤ 2 ጢሞ. 4፡22።

ለ. በመንፈሳችን እና በሌሎቹ የውስጥ ክፍሎቻችን መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ያስፈልገናል—መዝ. 51፡6፤ ሕዝ. 36፡26፤ 1 ጴጥ. 3፡4።

ሐ. ትክክል ሆነ ስህተት፣ ማንኛውንም ነገር በነፍሳችን ማድረግ በአሮጌው ሰው ውስጥ መኖር ነው፤ ስለዚህ፣ የነፍስ ሕይወታችንን፣ እኔነታችንን መካድ ያስፈልገናል—ማቴ. 16፡24-26።

መ. መንፈሳችንን ስንከተል ጌታን ራሱን እንከተላለን፣ ምክንያቱም ጌታ በመንፈሳችን ውስጥ ነውና—2 ጢሞ. 4፡22፤ 1 ቆሮ. 6፡17።

## IV. በሕይወት መርህ መሠረት ለመኖር የሕይወትን የውስጥ ስሜት መከተል ያስፈልገናል—ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ. 4፡18-19፤ ኢሳ. 40፡31፦

ሀ. የሕይወት ስሜት ውስጠ-ልምምዳዊ፣ የግል እና ተግባራዊ ነው፦
1. የሕይወት ስሜት በአሉታዊ ጎኑ የሞት ስሜት ነው—ሮሜ 8፡6።
2. የሕይወት ስሜት በአዎንታዊ ጎኑ ከብርታት፣ ከእርካታ፣ ከእረፍት፣ ከብሩህነት እና ከምቾት ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ጋር የሕይወት እና የሰላም ስሜት ነው—ቁ. 6።

ለ. የሕይወት ስሜት ምንጭ መለኮታዊው ሕይወት (ኤፌ. 4፡18-19)፣ የሕይወት ሕግ (ሮሜ 8፡2)፣ መንፈስ ቅዱስ (ቁ. 11፤ 1 ዮሐ. 2፡27)፣ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ መኖሩ (ዮሐ. 15፡4-5) እና እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ መሥራቱ (ፊልጵ. 1፡23) ነው።

ሐ. የሕይወት ስሜት አገልግሎት፣ የምንኖረው በተፈጥሮአዊው ሕይወት ወይም በመለኮታዊው ሕይወት መሆኑን፣ ወይም በሥጋ ወይም በመንፈስ መሆኑን እንድናውቅ ማድረግ ነው—1 ቆሮ. 2፡14-15፤ ሮሜ 8፡8-9፤ ገላ. 5፡16-17።

መ የአማኝ የሕይወት እድገት ከውስጣዊው የሕይወት ስሜት ጋር ባለው ልውውጥ ላይ ይመረኮዛል—ኤፌ. 4፡15፤ ቆላ. 2፡19፤ 1 ቆሮ. 3፡6-7።

ሠ. ወደ ሕይወት ስሜት ውስጥ ራሳችንን መጸለይ እና በቁጥጥሩ፣ በምሪቱ እና በአቅጣጫ-ሰጪ ንጥረ-ነገሩ ዕለት ዕለት መኖር ያስፈልገናል—ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ. 4፡18-19፤ 1 ዮሐ. 2፡27።

ረ. በመንፈስ መሠረት አብልጠን በተመላለስንና የሕይወትን ስሜት በተከተልን መጠን በሕይወት መርህ መሠረት አብልጠን እንኖራለን—ሮሜ 8፡4፣6።

## V. በሕይወት መርህ መሠረት ከኖርን፣ ነገሮችን የምንለየው ከትክክል እና ከስህተት አኳያ ሳይሆን ከሕይወት ወይም ከሞት አኳያ ነው—2 ቆሮ. 11፡3፦

ሀ. የዮሐንስ ወንጌል የሕይወት ዛፍ ክፉና መልካምን ከሚያስታውቀው የእውቀት ዛፍ ጋር እንደሚጻረር እና ለመልካም ወይም ለክፉ ሳይሆን ለሕይወት ግድ ሊለን እንደሚገባ አጽንኦት ይሰጣል—4፡10-14፣ 20-21፣ 23-24፤ 8፡3-9፤ 9፡1-3፤ 11፡20-27።

ለ. አንድን ጉዳይ ለመለየት ምርጡ መንገድ—የመለያው ምሥጢር—ከሕይወት ወይም ከሞት አኳያ መለየት ነው፤ ክርስቶስን እንደ የሕይወት አቅርቦታችን መደሰት የሚከለክለንን ማንኛውንም አይነት ንግግር በመቃወም፣ ነገር ግን ክርስቶስን እንደ አቅርቦታች ለመደሰት ሁልጊዜ የሚያበረታንን እውነተኛውን የጌታ አገልግሎት በመቀበል ነገሮችን በሕይወት እና በሞት መለየትን መማር አለብን—ሮሜ 8፡6፤ 2 ቆሮ. 11፡3።

© 2022 Living Stream Ministry